# መዝሙር እና የመዝሙር መሳሪያዎች

በዚህ ርዕስ ስለ ዜማ ስልት ስለ መዝሙር እና የመዝሙር መሳሪያዎች ስለ ቅዱስ ያሬድ መሠረታውያን የዜማ ስልቶችና ትርጉሜ ጠቅለል አድርጌ ለማብራራት ጥረት አደርጋለሁ።

## ስለ ዜማ ስልት

ዜማ ማለት ስልት ያለው ጩኸት ወይም በሥርዓት በደምብ የሚሰማ ድምጽ ሰሚውን የሚማርክ የሚመስጥ ለስሜት ትርጉም የሚሰጥ ድምጽ ማለት ነው። ቀሌምንጦስ እና አርጋኖን የሚባሉት የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ዜማ ከሰው አንደበት የሚወጣው ብቻ ሳይሆን ከወፎች የምንሰማው መልካም ድምጽም ሆነ ከዜማ መሳሪያዎች ቅኝት የምንሰማው ድምጽ ዜማ እንደሆነ ዜማም እንዳለው ዜማም እንደሚባል ይናገራሉ። የመጻሕፍቱ ቃል በግዕዝ እንዲህ ይላል። «አእዋፍ ዘሠናይ ዜማሆሙ ይሴብሕዎ በሠናይ ዜማ ወማኅሌት» ይህም ማለት «ዜማቸው ያማረ ወፎች በመልካም ዜማቸው ያመሰግኑታል» ማለት ነው። እንዲሁም «ኅብረተ ዜማ ዜማ ግዕዝ እዝል ወአራራይ ዝብጠተ መሰንቆ ወእንዚራ እለቦሙ ሠናይ ዜማ» ይላል። ሲተረጐም «በግዕዝ በእዝል በአራራይ የዜማዎች ኅብረት ዜማቸው መልካም ከሆነ ከመሰንቆና ከእንዚራ መደርደር (መመታት) ጋር ያመሰግኑታል» ማለት ነው። ( *ያሬድና ዜማው)*

ከዚህ በላይ እንዳየነው መልክና ስልት ያለው ጩኸት ሁሉ ዜማ አለው ዜማ ነው ዜማ ይባላል።

## የዜማ ክፍሎች

ዜማን በሁለት ክፍል ማየት እንችላለን።

፩. መንፈሳዊ ዜማ
፪. ሕዝባዊ (ዓለማዊ) ዜማ

**መንፈሳዊ ዜማ**

መንፈሳዊ ዜማ የምንለው በቤተ እግዚአብሔር እና እንዲሁም በዓበይት በዓላት በሕዝብ አደባባይ በእውነተኞች የዜማ ሊቃውንት በቅዱስ ያሬድ ደቀ መዝሙርት በድጓ በአቋቋም መምህራን የሚቀርብ የምስጋና ክፍል (አካል) ነው እውነተኛው ያሬዳዊ ዜማ። (መዝ 5፤3 መዝ 62፤6 መዝ 118፤62)

**ሕዝባዊ (ዓለማዊ) ዜማ**

ስልቱ የተወሰደው ምንጩና መገኛው መንፈሳዊ ዜማ ነው። ነገር ግን ስሙ እንደሚያመለክተው የሚውለው እንደ ሕዝቡ ባሕልና ሥርዓት ለዘፈንና ለልቅሶ ለዋይታ ለሽለላ (ለጃሎታ) ለቅርሮሽ (ቅርርቶ) ወዘተ ነው። ሕዝቡ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነ እንደሆነ «ሆ!» እያለም በሆታ ይዘምራል። እግዚአብሔርንም ያመልክበታል። ለምሳሌ በሀገራችን «ሆ! ነይ ነይ እምዬ ማርያም፤ በወት ግባ በወት ያገራችን ታቦት፤ ኤልያስ በሠረገላ፤ እረስይ አማኑኤል ...» ሌሎችም በሕዝብ ዜማ የሚቀርቡ የበዓል የሕዝብ ዜማዎች ናቸው። ዛሬ ዛሬ ግን ዳብሮና ሰፍቶ በልዩ ልዩ ሕዝባውያን ዘማሪዎች ተቀናጅቶ ሲዘመር ይታያል። ደስ የሚያሰኝ ነው።

ሕዝብ ከእግዚአብሔር የተለየ ከሆነ ግን በሕይወቱ ስለ አጋጠመው ገጠመኝ ስለ ሥጋ ፍላጐቱ ስለ ምኞቱ ይዘፍንበታል። በሌላም መልኩ ደግሞ ስለ ሀገሩ ስለ ወገኑ ያለውን ፍቅር ይገልጽበታል።
መንፈሳዊውም ሆነ ሕዝባዊው ዜማ በአንድ ነገር ይገናኛል። ሁለቱም መንፈሳዊው (አንደኛው) የሥጋንም የመንፈስንም ጉድለትና ክብር፤ ሞትና ሕይወት፤ ጽድቅና ኩነኔ ሌላም ሌላም ሲገልጽ ዓለማዊውም የዓለሙን ጉድለትና ምኞት በመግለጽ ሁለቱም የሰውን የውስጥ ስሜት በመግለጽ አንድ ይሆናሉ። ይዞታቸውና መልዕክታቸው ግን ፍጹም የተለያየ ነው።

ከሰው ልጅ ስሜት አንጻር ዜማ ሲታይ ከገነት የተለየ ከእግዚአብሔር የራቀ የሰው ልጅ በመቆዘም በማንጐራጐር በደሉን ማሰብ ማንነቱን ማስታወስ ከእግዚአብሔር እርዳታ መጠየቅ ብሶቱንም ማስታወስ ብሶቱንም መግለጽ የቻለበት መንገድ ነው። ከዚያ በፊት ግን (ከስህተት በፊት) መታከትን ድካምን በማያስከትል የምስጋና ቃል ሕይወቱ የተመላ ነበር። ከውድቀት በኋላ ግን እርዳታ ፈላጊ ሆነ። ጩኸቱን እንደ ሀገሩ ልማድ እና እንደ ጸጋው መጠን በልዩ ልዩ ሥነ ዜማ ማቅረብ ጀመረ። የተፈረደበትን ፍርድም ሆነ የተፈረደለትን፤ የተደረገለትን በጐ ነገርም ሆነ የተደረገበትን በዜማ መግለጽ ጀመረ። የዜማ መጻሕፍትም ዋና ማዕከላዊ አስተምህሮ የሰው ልጅ ሞትና ሕይወት፤ የእግዚአብሔር ፍርድና ምህረት ናቸው።

# <u>ያሬድዊ ዜማ</u>

ቅዱስ ያሬድ በቅዱሳት መጻሕፍቱ እውቀት የተራቀቀ ሊቅ፤ በጸጋ እግዚአብሔር የተቃኘ በሥነ መለኮት አስተምህሮው የላቀ ምጡቅ ሰው እንደ ነበር ድርሰቶቹም የቤተ ክርስቲያን ታሪክም ምስክሮች ናቸው። ቅዱስ ያሬድ ኅዳር ፭ ቀን ፭፻፴፬ ዓ. ም. ከሰማይ ድምጽ ሰምቶ ሀብተ ዜማ ተሰጥቶት አፄ ገብረ መስቀል በመስከረም ፲፯ ቀን ፭፻፴፬ ዓ. ም. ነግሰው እርሱ በኅዳር ከጣዕሙ ብዛት የተነሳ አዕጽምት (አጥንት) የሚያለመልም ዜማ ደርሷል።

<u>ጥቅስ በግዕዝ፤</u> «ወስምዐ በህየ ቃለ እንዚራ ወቃለ አርጋኖን ወቃለ መሰናቅው እንዘ ይሴብሕዎ ወይዌድስዎ ወየአኵትዎ ለፈጣሬ ሰማያት ወምድር በስብሐት ወበማኅሌት በቅኔ ወለልዑል ዜማ ነግሀ ወሠርከ ይሴብሕዎ ለንጉሥ ዐቢይ በዓውደ መንበሩ ቅዱስ ... አነ እነግረከ በዘትሌቡ ጸውዕ ስሞ ሐዲስ ለእግዚአብሔር ዝውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወትነስእ ማኅሌተ እምዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ በበዜማሁ ወይቤ ጐስዐ ልብየ ...»

<u>ትርጉም በአማርኛ፤</u> «በዚያም የእንዚራን፣ የአርጋኖን፣ የመሰንቆን ድምጽን እንደዚሁም ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ትልቁን ንጉሥ እግዚአብሔርን ጧትና ማታ በስብሐትና በማኅሌት (በቅኔ) ጧትና በሰርክ ከፍ ባለ ዜማ ካህናተ ሰማይ መላእክት በተቀደሰ ዙፋኑ ዙሪያ ሲያመሰግኑ ሰማ ... እንግዲያውስ እኔ የምታስተውልበትን እነግርሃለሁ። የእግዚአብሔርን አዲስ ስም ጥራ። ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይም በየአይነቱ ዜማ ያለውን ማኅሌት ታማራለህ የሚል ቃል ሰማ ... ልቤ መልካም ነገር አውጥቶ ተናገረ።» ብሎ ተናገረ የዜማ ሐብትም ተሰጠው። *(ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ ገጽ 23-24)* ተብሎ እንደተጻፈ።

## *ሦስቱ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ስልቶች*

- ❖ ግዕዝ፦ ግዕዝ ማለት የዜማ መጀመሪያ የመጀመሪያ ዜማ አንደኛ ቀዳሚ ማለት ነው።
- ❖ ዕዝል፦ ዕዝል ማለት በግዕዝ ላይ ታዝሎ ተደርቦ የሚዜም የሚዘመር ከባድ የበዓል የደስታ ቀን ዜማ ማለት ነው።
- ❖ አራራይ፦ አራራይ የሚያራራ፤ ልብ የሚመስጥ ትዝታ ተመስጦ የሚያስከትል ዜማ ማለት ነው።

ቅዱስ ያሬድ በእነዚህ የዜማ ስልቶች ላይ ተመስርቶ ስለ እግዚአብሔር መኖር፤ ስለ ፍጥረተ ዓለም፤ ስለ ምስጢረ ሥላሴ፤ ስለ ምስጢረ ሥጋዌ በአጠቃላይ ትምህርተ ሃይማኖትን፤ ነገረ መለኮትን፤ ክብረ ቅዱሳንን መሰረት አድርጎ በሰፊው ዘምሯል። አምስቱ የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍትም (ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ እና መስዋዕት) የሚያረጋግጡት ይህንኑ ነው።

## *<u>የመዝሙር መሳሪያዎች</u>*

የመዝሙር መሳሪያዎች ከየት መጡ?

1.<u>መለከት</u>፦ ከቀንድ፣ ከብረት እና ከብር የሚሰራ የእግዚአብሔር ጉባኤ መጥሪያ ለመዘመሪያ የሚያገለግል መሳሪያ ነው። አንዳንድ ጊዜ ቀንደ መለከት ይባላል ከቀንድ መሰራቱን ያመለክታል። መለከትን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሩት የቃየል ልጆች ናቸው። የተጠቀሙበትም መጀመሪያ እነሱ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው ለመጀመሪያ ጊዜ ከተማ የቆረቆሩ የተፈጥሮ ሕግ ሽረው ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት የጀመሩ የነፍስ ገዳዩ እና የቀበዝባዛው የእግዚአብሔር ልጆች ከመባል የሰው ልጆች ለመባል ያበቃው የእርጉሙ የቃየል ልጆች ናቸው። መለከትን የሰሩት በከተማቸው ሊዘፍኑበት ሊያንጐራጉሩበት ነበር። ከእግዚአብሔር የተለየች በሕገ ተፈጥሮ (ህሊና) ላይ ያመጸች ሞት የተፈረደባት ሕይወታቸውን ለማባበል የዜማ ዕቃ ልዩ ልዩ ነገሮችን እየቀጠቀጡ ይሰሩ ነበር። ምስጢሩ ግን በደለኛው ማንነታቸው (ሕይወታቸው) እርዳታ እየፈለገ ሰላም አጥቶ መቆዘምና ማንጐራጐር መጀመሩን ያመለክታል። ዛሬም አንድ ሰው በሰራው በኃጢአት ምክንያት የህሊና ሰላም እንደሚያጣ እና ሁከት እንደሚነግስበት እነሱም በአንደበታቸው ጩኸው ሊወጣላቸው ያቃታቸውን ከልባቸው የተረፈው የውስጥ ጩኸት በመሳሪያ እየታገዘ ይወጣ ጀመር።

እግዚአብሔር በተፈጥሮ ሰውን ለምስጋና እንጂ ለዘፈን አልፈጠረውም፤ የሚያዝነውም ሆነ የሚደሰተው የሚዘምረውም ሆነ የሚዘፍነው ሰው ያለው አንድ ስሜት ብቻ ነው። ሰው በቅጽበት ልዩነት ሊሆን ይችላል እንጂ በአንድ ጊዜ ደስታ እና ሐዘን አይሰማውም። ስሜቱ አንድ ብቻ ስለሆነ ግን እንደ ሁኔታው ስሜቱ ይለዋወጣል። ሰይጣን የሰው ልጆችን የተፈጥሮ ጸጋ የሆነውን የምስጋና ስሜት በመለወጥ ለብሶት ጩኸትና ለዘፈን እንዲጠቀሙበት ገፋፋቸው። ለእግዚአብሔር ክብር እንዳይዘምሩ በኃጢአት አውሮ ወንዱ ስለ ሴቶች ሴቶቹም ስለ ወንድ ማቀንቀን ጀመሩ። የእግዚአብሔር ፍቅርም ክብርም ከነሱ ራቅ በመሆኑም በዓለም የሰው ልጆችና የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የሰው ልጆች በሁለት ሲከፈሉ መለከትን ሰርተው ይጠቀሙ የነበሩት የእግዚአብሔር ልጆች የሴት ልጆች ሳይሆኑ የሰው ልጆች የተባሉ የቃየል ልጆች ነበሩ። *(ዘፍ ፬፤፳፩ ዘፍ ፮፤፪)*

በኋላ ግን መለከት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ዋለ የእግዚአብሔር ክብር ታወጀበት። የቃየል ልጆችም የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ናቸው። አእምሮንም ሰጥቶ የፈጠራቸው እግዚአብሔር ነው። ለሰይጣን የራሱ የሆነ ንብረት የለውምና የደከሙበት ዕቃ ለበጐ ዋለ። ሰይጣን በእግዚአብሔር ፍጥረት በደል ቢሰራ ያሳዝናል እንጂ እግዚአብሔር በኃጢአት

አልገዛልህም ያሉትን ቢገዛቸው የሚያስገርም አይደለም፤ ንብረቱ ናቸውና። የመለከት አገልግሎት የተገለጸባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከዚህ የሚከተሉ ናቸው። ዘኍ ፲፤፩-፲ ኢያሱ ፮፤፳ ፪ኛ ዜና ፭፤፲፪-፲፫ ፪ኛ ሳሙ ፮፤፲5 ፩ኛ ዜና ፲፭፤፳፰

2. <u>በገና</u>፦ አሥር አውታር ያለው የዜማ ዕቃ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሩት የተጠቀሙበትም እንደ መለከት ዘፋኞች የቃየል ልጆች ናቸው። ዘፍ ፬፤፳፩ ለዘፈን ብለው ሰሩት የሰው ልጆች (የሥጋና የደም ሥራ የሚሰሩ) ናቸውና ዘፈኑበት። (ዘፍ ፮፤፪) የእግዚአብሔር ልጆች ደግሞ ለመዝሙር ለምስጋና ተጠቀሙበት እኛም እንጠቀምበታለን። ቁምነገሩ ከሰሪዎቹና ከመሳሪያው ላይ ሳይሆን ከአጠቃቀሙ ላይ ነው። ልዩ የመዝሙር መሳሪያም ሆነ። ስለ በገና የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፦ ዘፍ ፬፤፳፩ ፩ኛ ሳሙ ፲፮፤፲፮-፳፫ ፩ኛ ዜና ፲፭፤፳፩ መዝ ፵፪፤፪ ራዕይ ፭፤፰

3. <u>ክራር</u>፦ የበገና ዓይነት የዜማ ዕቃ ነው። የዘመናችን ክራር ስድስት የጅማት አውታሮች አሉት። ክራርን በበገና ዓይን ካላየነው በቀር በክራር ሲዘመር እንደ ነበር ክራር የመዝሙር መሳሪያ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አጐላምሶ ጠቅሶት አናገኝም። በስም ግን ጠርቶት ይገኛል። ናቡከደነጾር ጣዖቱን ካሳጀበባቸው መሳሪያዎች አንዱ ክራር እንደሆነ ትንቢተ ዳንኤል ፫፤፭-፯ ተጠቅሶ እናነባለን። በ፩ኛ ቆሮ ፲፬፤፯ ላይም ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ልሳን ሲናገር ሕይወት የሌለች መሳሪያዎች ሲቃኙ እንደ ቅኝታቸው ስሜት የሚሰጥ ድምጽ ይሰጣሉ። እንዴት እናንተ በልሳን እናገራለን እያላችሁ ትርጉም የለሽ ነገር ትናገራላችሁ ብሎ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ግብዞች ባስተማረበት ክፍል ለምሳሌ ከጠቀሳቸው መሳሪያዎች ክራርና ዋሽንት ይገኙበታል። በተጨማሪ ክራር በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን (የአሁኑን ዘመን አይጨመረም) የጐላ የመዝሙር ቦታ ተሰጥቶት አልተነበበም፤ ይሁን እንጂ በክራር መዘመሩ በደል አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ግን ባትለየውም እውቅና አልሰጠችውም። በአሜሪካ ያሉት አባቶች ጉባኤ ቅዱስ ሲኖዶስም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉት አባቶች ጉባኤ ቅዱስ ሲኖዶስ በውሳኔው ውስጥ በተራ ቁጥር አልጠቀሰውም።

4. <u>ዋሽንት</u>፦ እንደ ክራር ናቡከደነጾር ጣዖት ካሳጀበባቸው መሳሪያዎች አንዱ ነው። ዳን ፫፤፭-፯ ፩ኛ ቆሮ ፲፬፤፯ ይሁን እንጂ ለሰይጣን ንብረት ስለሌለው እንደ አጠቃቀሙ ስለሆነ ለእግዚአብሔር ክብር መዋሉ ባይነቅፍም ቤተ ክርስቲያን ግን እውቅና ሰጥታ በዚህ አመስግኑ ብላ በውሳኔ አላስተላለፈችም። ዋሽንት በሀገራችን ባሕል የሕዝብ መጫዎቻ ነው። በመሆኑም የከበረ ዕቃ ነው።

5. <u>መቋሚያ</u>፦ በቅዱስ ያሬድ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመዝሙር የዋለ የዜማ ማሳያ የመዝሙር መሳሪያ ነው። የሚሰራውም ቀጥ ባለ እንጨት ሆኖ ጫፉ ላይ የቀንድ የብር የነሐስ የብረት የእንጨት መያዣ (መደገፊያ) ያለው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጠቀሰም እግዚአብሔር በየዘመናቱ አዳዲስ ጸጋ ለሰዎች ስለሚሰጥ ለአባቻችን ለቅዱስ ያሬድ የሰጠው ልዩ የሚመስገኛ ዘንግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመቆሚያ አመስግኑት አላለም ብለን የእግዚአብሔርን ጸጋ ልንቃወም አንችልም በየዘመኑ አዲስ ጸጋ የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና። ቅዱስ ያሬድ በዚህ ዘመን ተነስቶ ቢሆን ግን መቋሚያህን አስቀምጥ የሚሉ ከሳሾች በተነሱበት ነበር።

6. <u>ከበሮ</u>፦ ፍጹም ለእግዚአብሔር ክብር የዋለ የመዝሙር ዕቃ ነው። ለድል ቀን መታሰቢያ ይመታ ነበር። ዘጸ ለ፭፤፳ ለእግዚአብሔር ክብር መዝሙር የሚቀርብበት መሳሪያ ነው። መዝ ፩፻፵፱፤፬ ለታቦት ክብር ይዘመርበታል። ፩ኛ ሳሙ ፲፰፤፮ ፪ኛ ሳሙ ፮፤፭ በአንጻሩም የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ሲያመሰግንበት ዓለም ደግሞ ወስዳ ትዘፍንበታለች። ያ ግን የከበሮን አገልግሎት ክብር አይቀንሰውም።

7. <u>ጸናጽል</u>፦ ሁለት ዓይነት ጸናጽል አለ። አንደኛው የማጨብጨቢያ ጸናጽል (ናቁስ) ይባላል። እንደ መረዋ ያለ ነው ይላሉ አበው። አሁን እኛ ዛሬ አንጠቀምበትም መሳሪያውም የለንም። ሁለተኛው አሁን የምንጠቀምበት ዓይነት ጸናጸል ነው። ከነሐስ ከብር ይሰራል። ጸናጽል የተቀደሰ የመዝሙር መሳሪያ ነው። ፪ኛ ሳሙ ፮፤፭ መዝ ፩፻፶፤፭ ፩ኛ ዜና ፲፫፤፰ ፪ኛ ዜና ፭፤፲፫ ፩ኛ ቆሮ ፲፫፤፩

8. <u>መሰንቆ</u>፦ «ሰንቀወ» ሰነቃ፣ ሞዘቀ፣ መታ፣ አስጮኸ፣ ደረደረ። ከረከረ ከመሳሪያው ጋር ጮኸ፣ አዜመ፣ ዘመረ፣ ገጠመ፣ አጉረመረመ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ነው። ግሩም የመዝሙር መሳሪያ ነው። ኢሳ ፭፤፲፪ ኢዮ ፳፩፤፲፪ ኢሳ ፳፫፤፲፮ ሲራክ ፳፪፤፮ ዮዲት ፲፮፤፩ መዝ ፩፻፶

9. <u>እንዚራ</u>፦ «እንዘረ» መታ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ይመስላል። ግን አንዳንድ መጻሕፍት የሚመታ መሳሪያ ሳይሆን በእስትንፋስ የሚነፋ መሳሪያ እንደ ሆነ ያመለክታሉ። የእንዚራን ትክክለኛ መልክ እስከ አሁን ማግኘት አልተቻለም። አንድ አንድ አባቶች ደግሞ እንዚራ «አኮርዲዮን» ነው ይላሉ። ለማንኛውም ቃሉ በመጽሐፍ ተጠቅሷል። «ሰብሕወ በከበሮ ወበእንዚራ» (መዝ ፩፻፶)። «እንዚሁ ለበኩርኪ» (አባ ጊዮርጊስ) «እለይነፍሑ እንዚራተ» (ፍትሐ ነገሥት ፳፫) ዛሬ ይህ ነው ተብሎ በቅርብ አግኝተን ባንጠቀምበትም እንዚራ ልዩ ግሩም የመዝሙር መሳሪያ እንደሆነ እንማራለን (እንገነዘባለን)።

10. <u>እምቢልታ</u>፦ ታላቅ ዋሽንት ውስጡ ክፍት የሆነ የጥንት ዘመን ነገሥታት መኳንንት ደጃዝማች ብቻ ይጠቀሙበት

የነበር ከቀርቅሐ ወይንም ከሸንበቆ የሚሰራ ነው። በብሉይ ኪዳን የታወቀ የመዝሙር መሳሪያ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች፡- ፩ኛ ዜና ፲፭፥፳፰ መዝ ፩፻፶፥፬ ኢዮብ ፳፩፥፲፪ ኢዮብ ፴፥፴፩። አሁንም በሀገራችን በትልልቅ አድባራት ለምስጋና ሲውል ይታያል። የከበረ የመዝሙር መሳሪያ ነው። ከዋሽንት ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ዋሽንትም በእንቢልታ ዓይን ስለሚታይ ሳይሆን አይቀርም መዝሙር የሚቀርብበት።

11. <u>አርጋኖን (ኦርጋን)</u> ስያሜው፡- አርጋኖን … በግዕዝ
ኦርጋኖን … በግሪክ
አርቀኑን … በአረብኛ
ኡጋቡ … በዕብራይስጥ
ኦርጋን … በእንግሊዝኛ

(የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የግዕዝ መዝገበ ቃላትን ይመልከቱ)

<u>ኦርጋን</u> የመዝሙር የማኅሌት የዘፈን የዜማ ዕቃ ነው። አርጋኖን/ኦርጋን የተሰራው ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ በናይል (በአባይ) ወንዝ አጠገብ በእስክንድሪያ በአንድ ግሪካዊ ዝርያ ባለው ሰው ነው። የተሰራበት ዘመንም ከክርስቶስ ልደት በፊት (በብሉይ ኪዳን ዘመን) ሦስት ዓመት ቀድሞ ነው። ስለዚህም ስለ ኦርጋኖን/አርጋን ታሪክ የተጠና ጥናት እንዲህ ይላል። ኦርጋን/አርጋኖን ቀስ በቀስ እያደገ እየተቀናጀ ይምጣ እንጂ ከጥንት ጀምሮ ነበር። በኋላ ግን ልዩ ልዩ ክፍል ያለው "mouth organ, pipe organ, etc…" እየተባለ የሚጠራ
እንዲሁም church organ የሚባለው ልዩ መሳሪያ ከጥንት ጀምሮ እንደነበረ ታሪክ ያሳያል። "Greek engineer working in Alexandria in the third century BC … which the organ was known in red, beginning in the Nile Delta region around Alexandria …" ይላል። (Organ History page 2-5)

ጥናቶች ሁሉ እንደሚያመለክቱት ኦርጋን/አርጋኖን ጥንታዊ የዜማ ዕቃ ነው። በዘመናችን ያሉ አንድ አንድ ሰዎች በዘመናዊ መሳሪያ አንዘምርም ለማለት ከሚጠቅሷቸው ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች «ምዕራባዊ ነው» እና «ዘመናዊ ነው» የሚሉ አስተሳሰቦች ሲስነዘሩ ይሰማሉ። በመሰረቱ በመቼም ይሰራ የትም ይሰራ አንድን ነገር ለመቀበል የሚከለክል ነገር የለም። ግን ታሪክ እንደሚያስረዳው ምዕራቡ ዓለም ለእድገቱ የሚጠቅሙትን ጥበቦች ከግሪክ እና ከአፍሪካ ለቃቅሞ ሲወስድ አብሮ የወሰደው መሳሪያ እንጂ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራው አባይ ወንዝ አጠገብ ነው።

ሮም በወደቀች ምስራቅ ኤሮፕ ባደገች ጊዜ በቤዘንታይን ዘመነ መንግሥት እንዲሁም ቤተ ቤርስቲያን ከመከፋፈልዋ በፊት በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት አርጋኖን/ኦርጋን ልዩ የእግዚአብሔር ስም መቀደሻ የዲያቢሎስ ድል መንሻ የመዝሙር መምነሽነሽያ መሳሪያ እንደ ነበር ጥናቶች ያሳያሉ። የኛ አባቶች እነ ቅዱስ ያሬድ እነ አባ ጊዮርጊስም ስለ አርጋኖን/ኦርጋን ጣዕም ብዙ ዘምረው ጣዕሙን ተናግረው በመጻሕፍቶቻቸውም ጽፈው ምሳሌም መስለውበት እናገኛለን። ኢትዮጵያ ሀገራችን የዛሬን አያድርገውና ከነአውሮፓ በፊት የሰለጠነች ግሪክን ግብጽን በሥልጣኔ የምትመስል ሀገር ስለነበረች የኦርጋኖን/የኦርጋን አገልግሎት በኢትዮጵያ የታወቀ እንደነበር የሚያጠራጥር አይደለም የተፈጠረው እራሱ አባይ ዳር ነውና። ግን ደሃን ሲያጣ ማንም አይወደውምና ታሪኩን ሁሉ ባዕዳን ስለወሰዱት እንኳን አርጋኖን መሰንቆው ሁሉ ከዕቃ ቤት ስለተባረረ እኛም የኛ ሳይመስለን ምእራባውያንም የኛ ነው ለማለት ሲከጅሉ ይታያል። ግን ምሑራን አልተቀበሏቸውም። በጥናታቸውም አፍሪካዊ የአባይ ዳር ግኝት የዜማ ዕቃ እንደሆነ ጽፈዋል።

## <u>የቅዱስ ያሬድ እና የአባ ጊዮርጊስ ምስክርነት</u>

<u>ቅዱስ ያሬድ ስለ አርጋኖን/ኦርጋን ምን አለ?</u>

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መልካም ነገርን ሁሉ በምሳሌ ይጠቀሙበታል። አባታችን ቅዱስ ያሬድ ወንጌላዊ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድን እያስታወሰ በዘመረበት ክፍል የቅዱስ ዮሐንስን አስተምህሮ ጣዕም የቃሉን መዓዛ ለመግለጽ ከተጠቀመባቸው አንዱ አርጋኖን/ኦርጋን ነው። ለምሳሌ እመቤታችንን ቅዱስ ኤፍሬም ቅዱስ ሕርያቆስ በመሰንቆ በጸናጽል በበትረ አሮን እየመሰሉ እንደተናገሩት ያለ ነው።
ጥቅስ በግዕዝ፥
1) «ሰባኬ ወንጌል ዮሐንስ አርጋኖን ትንቢት ዘይድምጽ ለቤተ ክርስቲያን»

<u>ትርጉም፥</u>
«ሰባኬ ወንጌል ዮሐንስ ለቤተ ክርስቲያን መልካም ድምጽ የምትሰጥ በትምህርትህ የምትመሰጥ የቤተ ክርስቲያን ኦርጋን/አርጋኖን ነህ።» ይላል ቅዱስ ያሬድ። (ዚቅ የጥር ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ እስመ ለዓለም)

<u>ጥቅስ በግዕዝ፥</u>
2) «ከመዝብጠተ መሰንቆ አርጋኖን ስብሐቶሙ ለእሙንቱ ካህናት»

**ትርጉም፥**

«የካህናቱ ምስጋና መሰንቆ አርጋኖን ሲመታ እንደሚመስጠው ድምፅ ጣፋጭ ነው» ይላል ቅዱስ ያሬድ። (አርያም ዘቅዱስ ያሬድ የማክሰኞ ገጽ ፩፻፶፪)

ከዚህ በተጨማሪ ቅዱስ ያሬድ ለመጀመሪያ ጊዜ ዜማን ሲደርስ ከሰማቸው የዜማ ዕቃ ድምፆች አንዱ የኦርጋን ድምጽ እንደነበር ገድለ ያሬድ ይናገራል።

**ጥቅስ በግዕዝ፤**

3) «ወስምዐ በሀየ ቃለ እንዚራ ወቃለ አርጋኖን ወቃለ መሰናቅው እንዘ ይሴብሕዎ ወይዌድስዎ ወየአኩትዎ ለፈጠሬ ሰማያት ወምድር በስብሐት ወበማኅሌት በቅኔ ወበልዑል ዜማ ነግሀ ወሠርከ ይሴብሕዎ ለንጉሥ ዐቢይ በዓውደ መንበሩ ቅዱስ … »

**ትርጉም በአማርኛ፤**

«በዚያም የእንዚራን፣ የአርጋኖን፣ የመሰንቆን ድምጽን እንደዚሁም ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ትልቁን ንጉሥ እግዚአብሔርን ጧትና ማታ በስብሐትና በማኅሌት (በቅኔ) ጧትና በሰርክ ከፍ ባለ ዜማ ካህናተ ሰማይ መላእክት በተቀደሰ ዙፋኑ ዙሪያ ሲያመሰግኑ ሰማ … » *(ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ ገጽ 23-24)*

ከዚህ በላይ እንዳየነው አርጋኖን ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን የነበረ አሁን ግን ስሙን እንጂ መልኩን፤ ዜናውን እንጂ ግብሩን ባለማገናዘብ በአርጋኖን እንዘምራለን «በኦርጋን» አንዘምርም የሚሉ ሰዎች አሉ። ግን ከበሮ እዘምራለሁ «በድራም» አልዘምርም፤ ውኃ እጠጣለሁ «ዋተር» አልጠጣም እንደማለት ነው። አርጋኖን ኦርጋን ነውና።

**አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ስለ አርጋኖን/ኦርጋን የተናገሩት ምንድን ነው?**

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ጥንት ለኮመልዝ ይባል በነበረው ዛሬ ወሎ በሚባለው ክፍል ሀገር አማራ ሳይንት ልዩ ስሟ ሾግለ ከሚባል ቦታ ነው የተወለዱት። አባታቸው ሕዝበ ጽዮን እናታቸው እምነ ጽዮን ይባሉ ነበር። በ፲፫ሺህ፻፶፯ ዓመተ ዓለም (በ፲ሺህ ፫፻፶፯ ዓ.ም. ጥቅምት ፫ ቀን ተጸንሰው ሐምሌ ሰባት ቀን ተወለዱ። በትምህርት በገዳማዊ ሕይወት አድገው ብዙ መጻሕፍት ጽፈዋል። ከመጻሕፍቶቻቸው መካከል «አርጋኖን» እና «እንዚራ ስብሐት» የሚባሉ ይገኙባቸዋል። እነዚህ መጻሕፍት በመዝሙር መሳሪያዎች ስም የተሰየሙ ናቸው። በአጠቃላይ አባ ጊዮርጊስ ከአሥር በላይ መጻሕፍት ደርሰው ተጋድሏቸውን ፈጽመው በ፲ሺህ፬፻፲፫ ዓ.ም. አርፈዋል። አባ ጊዮርጊስ ከተነሱበት ዘመን ትንሽ ቀደም ብሎ በአሥረኛው ምእተ ዓመት የኦርጋን አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን በሰፊው ይሰጥበት የነበረበት ዘመን ነበር። (Orthodox Dictionary of The Christian Church page 1192)

አባ ጊዮርጊስም የመዝሙር መሳሪያው የአርጋኖኑን/የኦርጋኑን ድምጽ እያስታወሱ ስለ እመቤታችን ምስጋና ሲያዘጋጁ በዘመናቸው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጣዕም ያለው ውዳሴ ይቀርብበት በነበረው በአርጋኖን/በኦርጋን መስለው የምስጋናውን ጣዕም እንደ አርጋኖን/ኦርጋን የውዳሴ የቅዳሴ የመዝሙር መሳሪያ ለዛ ያለው እንዲሆን በማሰብ መጽሐፉን አርጋኖን ብለውታል። እመቤታችንንም በአርጋኖን/ኦርጋን መስለዋታል። መጽሐፋቸውን (አርጋኖን) መጻፍ ሲጀምሩ እንዲህ አሉ፥

**ጥቅስ በግዕዝ፥**

1) «ንጽህፍ እንከ ዘንተ መጽሐፈ ዘይሰመይ አርጋኖነ ውዳሴ ወመሰንቆ መዝሙር ወእንዚራ …»

**ትርጉም፥**

«የምስጋና አርጋኖን/ኦርጋን የመዝሙር መሰንቆ እንዚራም የሚባል ይህንን መጽሐፍ መጻፍ እንጀምራለን …» ብለው መጽሐፉን ጀምረዋል። ኦርጋን መሰንቆ እንዚራ የማመስገኛ መሳሪያዎች ጣዕም ያለው ድምጽ እንደሚሰጡ አባ ጊዮርጊስ የደረሱት የጸሎት መጽሐፍ ነፍስን የሚያስደስት በመሆኑ መጽሐፉን በአርጋኖን/በኦርጋን በመሰንቆ በእንዚራ ቃሉን በመሳሪያዎቹ ድምጽ መስለው ተናግረዋል። (አርጋኖን ዘሰኑይ ገጽ 9)

**ጥቅስ በግዕዝ፥**

2) «… ወከማሁ ሊተኒ ርድአኒ ሊወጢነ ጽሒፈ ውዳሴሃ ለመርዓተ አብ ወአስልጥነኒ ከዕበ ለፈጽሞቱ ወለከናፍርየኒ ወአፉየ ረስዮን ከመአርጋኖን ወኃይለ መንፈስ ቅዱስ ይዝብጦን ዘበልሳን ከመይንብባ ዘይኤድምሙ ለሰማዕያን መረስዮ ለአፉየ ከመመሰንቆ ወድኅንጻ መንፈስ ይጉድኦ ከመይንቁ ሐዋዘ ወይሰንቁ ምዑዘ። ወእለ ያጸምኡ ይኩኑ ፍሡሓነ በሰሚኦቱ ይትመሰጥ ህሊናሆሙ ላእለ ወአኮ ታህተ የሀልዩ ጽድቀ ወአኮ ኃጢአተ የሀልዩ ንጽሐ ወአኮ ርስሐተ የሀልዩ ይዋሄ ወአኮ ጽልሁተ የሀልዩ ትህትና ወአኮ ትእቢተ የሀልዩ ፍቅረ ወአኮ ቅንአተ የሀልዩ ልባዊ ወአኮ እበደ የሀልዩ ክብረ ወአኮ ሀሳረ የሀልዩ ዘኢይማስን ወአኮ ዘይማስን የሀልዩ ዘኢይበሊ ወአኮ ዘይበሊ የሀልዩ ዘበሰማይ ወአኮ ዘበምድር …»

**ትርጉም፥**

የአብ ሙሽራ የሆነችውን (የድንግልን) የምስጋና መጽሐፍ መጻፍ እንድችል እርዳኝ። ለመፈጸምም እንድበቃ ሥልጣኑን ስጠኝ። ከንፈሮቼን እና አንደበቴን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በልዩ ቋንቋ ሰሚዎችን ደስ የሚያሰኝ ነገር ይናገሩ ዘንድ እንደ አርጋኖን/ኦርጋን አድርግልኝ። አንደበቴም እንደ መሰንቆ መልካም ሆኖ ይዘምር ዘንድ ምኡዝ ጣዕም ለዛ ያለው ድምጽ ይሰጥ ዘንድ ድህንፃ መንፈስ/የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደ መሰንቆ አንደበቴን ያጫውተው (ይምታው)። አርጋኖን/ኦርጋን መሰንቆ ሰሚዎቻቸውን ደስተኛ እንደሚያደርጉ እነርሱን የሰሙ በመሳሪያዎቹ ድምጽ እንደሚመሰጡ ይህንን የእመቤታችንን ውዳሴ የሚሰሙ ኅሊናቸው ይማረክ። ኃጢአትን ያይደለ ጽድቅን ያስቡ፤ ርስሐትን ያይደለ ንጽህናን ያስቡ፤ ቅንአትን

ያይደለ ፍቅርን ያስቡ፤ ስንፍናን ያይደለ ጥበብን ያስቡ፤ ውርደትን ያይደለ ክብርን፤ የሚያልፈውን ያይደለ የማያልፈውን፤ የሚያረጀውን ያይደለ ያለውን፤ በምድር ያለውን ያይደለ በሰማይ ያለውን ያስቡ ...» ማለት ነው። (አርጋኖን ፲፩-፲፪)

አባ ጊዮርጊስ ከዚህ ሌላም መሰንቆ የሚሰነቃ መሳሪያ ለመሆኑ፤ እንዚራ ደግሞ የድምጽ፣ የእስትንፋስ መሳሪያ ስለመሆኑ አርጋኖን/ኦርጋን ደግሞ በእጅ የሚነቃቃ የጣት መሳሪያ ለመሆኑ በልዩ ልዩ ስልት «እሴብሕ ፀጋኪ» በተባለው የዘወትር የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ላይ ተናግረዋል።

1) ስለ መሰንቆ እንዲህ አሉ፥

__ጥቅስ በግዕዝ፥__
«ምንት ረበሑ ለመሰንቆ ለእመ አልቦ ዘይሰነቅሖ»
__ትርጉም፥__
«የሚሰነቃው፣ የሚመታው፣ የሚከረከረው፣ የሚሞዝቀው ከሌለ የመሰንቆ ጥቅሙ ምንድን ነው።» ይላል።
ለዚህም የተጠቀሙት የግዕዝ ቃል «ሰንቀወ» ሰነቃ መሰንቆ መታ የሚለውን መሆኑን አንባቢ ልብ ይበል።

2) ስለ እንዚራ ደግሞ እንዲህ አሉ።
__ጥቅስ በግዕዝ፥__
«ወምንተ ይደምጽ ንቃወ እንዚራ ዘሰቁል ለእመ ኢተነፍሀ በድግታተ ማኅሌት» ይላል።
__ትርጉም፥__
«የተሰቀለው እንዚራ በአንድነት ካልተነፋ የእንዚራ ድምጽ እንዴት ሊሰማ ይችላል?» ማለት ነው።
ከዚህ ላይ እንዚራ የእስትንፋስ መሳሪያ ለመሆኑ አባ ጊዮርጊስ «ለእመኢተነፍሀ» ብለው ነፍሀ (ነፋ) በሚል ገላጭ አንቀጽ ስለገለጹት ልዩ መሳሪያ መሆኑን አንባቢ ልብ ይበል። «ድርገተ ማኅሌት» ማለት ደግሞ በዜና መዋዕል እንደተጻፈው ልዩ ልዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የሚጫወቱ ሰዎች በሕብረት በሚያቀርቡት የዜማ ድግስ ላይ እንዚራ የእስትፋስ መሳሪያ ሆኖ የሚቀርብ የድግስ አካል መሆኑን ያመለክታል።

3)ስለ አርጋኖን/ኦርጋን ደግሞ እንዲህ ብለዋል።
__ጥቅስ በግዕዝ፥__
«በነቀልቃለ ስብሐት ሑኪዮ ለአርጋኖነ ኅሊናየ ከመኢያርምም እምስብሐታተ ፍቅርኪ» ይላል።

__ትርጉም፥__
«የፍቅርሽን ምስጋና ከማቅረብ አንደበቴ ዝም እንዳይል አርጋኖን/ኦርጋን ኅሊናዬን [ልቤን] በምስጋና ስሜት ንውጽውጽታ አንቀሳቅሽው/ አናውጭው» ማለት ነው።
«ነቀልቃል» የወጣበት «አንቀልቀለ» የሚለው የግዕዝ ግሥና «ሑኪዮ» የሚለው አንቀጽ አርጋኖን/ኦርጋን በጣት ንውጽውጽታ መልካም ድምጽ የሚሰጥ መልካም የዜማ የመዝሙር መሳሪያ መሆኑን ስሙን ከነግብሩ ከነአፈጻጸሙ የሚገልጽ ነው።

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው በጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ቤርስቲያን የአርጋኖን/የኦርጋን አገልግሎት የነበረ ለመሆኑ ማስረጃ ነው። ከመልካም ጣዕሙም የተነሳ ቅዱሳን መልካም በሆነ ነገር ሁሉ እየመሰሉ እመቤታችንን ሲያመሰግኑ በዚሁ የዜማ ዕቃም መስለው ድንግልን አመስግነዋት አልፈዋል። ዛሬም ቤተ ክርስቲያን የመዝሙር መሳሪያዎችን ስትቆጥር አርጋኖን ብላ በቋንቋዋ ኦርጋንን አብራ በውሳኔዎች ውስጥ ጠቅሳዋለች። አንድ አንድ ዓይነ ልቡናቸው የታወረ ሰዎች ተነስተው ቤተ ቤተርስቲያንን ግራ ለማጋባትና የያዘችውን ለማስጣል ደፋ ቀና ማለት ከመጀመራቸው ቀደም ሲልም አርጋኖን/ኦርጋን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልዩ የምስጋና የቅዳሴ የውዳሴ መሳሪያ ሆኖ በታላላቅ አድባራት እግዚአብሔር ሲመለክበት ቆይቷል። ዛሬ ዛሬ ግን ቤተ ክርስቲያንን የምስጋና መሳሪያዋን እኛ እናውቅልሻለን፤ በዓለም የምንዘፍንበት ይህ ስለሆነ ይህንን ለዘፈን ተይልን፤ ዝም ብለሽ ተቀመጭ ብለው በጨዋ አንደበታቸው ቤተ ክርስቲያንን በማውገዝ አርጋኖን እንዳይዘመርበት ሲያከላክሉ በአርጋኖን/ ኦርጋን መዘመር እንደ አንቀጸ ሃይማኖት ታይቶ ሊቃውንት በጨዋዎቹ፤ ጳጳሳት በነጋዴዎች ሲወገዙ መስማት እየተለመደ መጥቷል።

በመሰረቱ በኦርጋን መዘመር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በአርመን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እና በህንድ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተለመደ የነበረ ያለ ነው። አሁን አሁን ግን የኛዎቹ ቢጽ ሐሳውያን ቤተ ክርስቲያን ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ወዲህ እንኳን ከ35-40 ዓመታት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እግዚአብሔርን ስታመልክበት ከኖረች በኋላ ማኅበርተኞች ለግላቸው በግላቸው ለቢዝነስ ያቋቋሙትን ማኅበር ይጻረርብናል ብለው የገመቱትን እና እንደ ጉባን ያዩትን

ሃይማኖተ አበውን እና የቅድስት ሥላሴን ሰንበት ትምህርት ቤት ለማጥፋት ከተጠቀሙባቸው መንገዶች እንደ አንድ አማራጭ አድርገው የወሰዱት ኦርጋንን ማስወገድ ነበር። (ይህ ራሱን የቻለ ታሪክና ምክንያት ያለው በመሆኑ ወደፊት አብራርቼ እጽፋለሁ።)

**<u>ልዩ ጥቅስ</u>**

**ግእዝ፥ «ሰብሕዎ በከበሮ ወበትፍስሕት**
**ሰብሕዎ በአውታር ወበእንዚራ»**

**አማርኛ «በከበሮና በዘፈን አመስግኑት**
**በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት»** ....**መዝ ፩፻፶፥፬**

English:
"Praise Him with the tumbrel and dance praise Him with stringed instruments and organ" *Psalm 150:4 … King James Version*

## <u>በአርጋኖን ላለመዘመር የፈለጉ ሰዎች የሚያቀርቧቸው ምክንያቶችና መልሶቻቸው</u>

1) **«በኦርጋን ዳዊት አልዘመረም። ሁሉ ተገልጾለት ትንቢት ሲናገር ወደፊት ኦርጋን እንሚሰራ ተገልጾለት ትንቢት አልተናገረም ...» ይላሉ።**

**እንደነዚህ ሰዎች ሃሳብ በዳዊት ዘመን ባልነበረ መሳሪያ ወይንም ዳዊት እንደ ምስጢረ ሥጋዌው ሁሉ ትንቢት ባልተናገረለት መሳሪያ መዘመር መጠቀም ስሕተት ነው። በመሰረቱ ነቢያት ኃላፍያት (ያለፉት) ቀደምያት መጻዕያት (የሚመጡት) ሁኔታዎች ተገልጸውላቸው መናገራቸው እውነት ነው። ግን ሃብተ ትንቢታቸው የተመሰረተው መንፈሳዊ ነገር በሚከናወንባቸው መሳሪያዎች ላይ ሳይሆን በምስጢረ ሥጋዌ በክርስቶስ ቀዳማዊ እና ዳግማዊ ምፅአቶች ላይ በአጠቃላይ በብሉያትና በሐዲሳት በተጠቀሱት ተስፋዎች ላይ የተመሰረተ ነው።**

**ይህንን ዓይነት ነገር የሚናገሩ ሰዎች በስልክ እንደሚያወሩ፤ በመኪና እንደሚሄዱ፤ በኢንተርኔት እንደሚገናኙ፤ በአውሮፕላን እንደሚበሩ ዳዊት ትንቢት ስላልተናገረ እነዚህን ነገሮች መጠቀም የለባቸውም ማለት ነው። በእርግጥ እነሱ ቤተ ክርስቲያንን ከምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት ለይተው ስለሚመለከቷት የእነርሱ የክርስትና ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ ስለሆን ነጠላውም መንፈሳዊ መስሎ መታየቱም ከዚያው ከቤተ ክርስቲያን ብቻ በመሆኑ ውጪ እንዘፍንበታለን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን አናመልክበትም እንደሚሉ ጥርጥር የለውም።**

**ሌላው ቅዱስ ያሬድ በመቋሚያ የዘመረው ዳዊት ስለ መቋሚያ ትንቢት ተናግሮ አይደለም እግዚአብሔር ገልጾለት ነው እንጂ። አንድ አንድ ጊዜ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኦርጋን አልተጻፈም ይላሉ። ስለ መቋሚያስ የት ተጽፏል? በዋሸንት ዘምሩ የሚልስ የት ይገኛል? መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወት መልእክት ላይ የተመሰረተ መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔር ወደፊት አዲስ ነገር በሰዎች ሕይወት ስለማይሰራ እንዳትጠቀሙ አላለም። መጽሐፍ ቅዱስ በኦርጋን አትዘምሩበትም አላለም። የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትም በአርጋኖን/በኦርጋን እናዳይዘመር አይከለክልም። አታዘምሩ የሚል ሳይሆን ዘምሩ የሚል ሥርዓት ነው ቤተ ክርስቲያን ያላት። ከጥንት ጀምሮ ኦርጋን የቤተ ክርስቲያን መሳሪያ ነውና።**

2) **«የዘፈን መሳሪያ ስለሆነ አንዘምርበትም ...»**
**ምነው ታዲይ መለከትን በገናን ክራርን ለዘፈን በዘፋኞች የተሰሩ ለሥጋ ፈቃድ የተቀጠቀጡ የዘፈን ዕቃዎች የጣዖት ማጀቢያዎች አልነበሩምን? በመሰረቱ ችግሩ ከዕቃዎቹ ላይ ሳይሆን ከተጠቃሚዎቹ እና ከአጠቃጠማቸው ላይ ነው። እግዚአብሔር ለምስጋና እንጂ ለዘፈን ስላልፈጠረን በኦጋርን ልንዘምርበት እንጂ ልንዘፍንበት አይገባም። ቤተ ክርስቲያንም ለዘፈን እውቅና አትሰጥም። እነ ከበሮም እነመሰንቆም እኮ ጠጅ ቤት ገቡ። አንዘምርባቸውም ልንል ነው?**

3) **«ባሕላች አይደለም የምዕራባዊያን መሳሪያ ነው ...»**

**በመሰረቱ ኦርጋን/አርጋኖን አፍሪካዊ ግኝት የቤተ ክርስቲያን ሃብት ቀደም ሲል እንደተመለከትነው እነ ቅዱስ ያሬድ ጣዕሙን ያደነቁት፤ እነ አባ ጊዮርጊስ የተመሰጡበት፤ በኢትዮጵያ ጥንታዊ የሥልጣኔ ዘመን የማኅሌት ሀብት ንብረት ሆኖ የነበረ፤ እነመሰንቆ እነበገና እነመለከት ከዕቃ ቤት ሲሰደዱ አብሮ ወጥቶ የቀረ ስሙ በዜማና በጸሎት መጻሕፍት እየታወሰ የሚገኝ ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ሀብት እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ምስክሮች ናቸው።**

**በመሆኑም ምዕራባውያን ከእስክንድርያ (ከኢትዮጵያ) ወሰዱት እንጂ እኛ ከእነሱ አላመጣነውም። ግን እነሱ ከአፍሪካ**

ወስደው አሳድገው ንብረታቸው አስመስሉት። በጥቁር ሕዝብ ላይ ነጭች የፈጸሙትን ግፍ ያየ ያነበበ ወጣት ሀብቱን በባሪያ ፈንጋዮች ዓይን በመመልከት ፈራው። «እባብ ያየ በልጥ በረየ» እንዲሉ። ያ ግን ያላደገ አስተሳሰብ ውጤት እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ጥንታዊ ታሪክና ሥርዓት የኦርጋንንም የመዝሙር መሳሪያነት የሚያጠፋ አይደለም። ለዚህም ከዚህ በፊት ያነበብነው መረጃ በቂ ነው።

4) «ከበሮን ጸናጽልን እና መቋሚያን ከቤተ ክርስቲያን ለመጥፋት ነው»

የሚያሳዝነው ሰው ስላማያውቀው ነገር ሲናገር መሰማቱ ነው። ለመሆኑ ማነው ስለዚህ ነገር ሊያስብ የሚገባው? በእርግጥ ማንም እንደ ክርስቲያንነቱ ማሰብ የሚገባውን ማሰብ ይቻላል። ግን ከላይ የተጠቀሱትን የመዝሙር መሳሪያዎች ድርሻ የሚወስድ አይደለም። ለሁሉም ጊዜ የአጠቃቀም ስልት መፍጠር ስለሚቻል እና ስለተቻለ የመሰንቆ መኖር ከበሮን እንደማያጠፋ የአርጋኖንም መኖር ከላይ ያሉትን አያጠፋም።

በተለያዩ ጊዜያት ወደ ቤተ እግዚአብሔር የገቡ ንዋየ ቅድሳት የየራሳቸው ድርሻ እና ጥቅም አላቸው። አንዳቸው ያንዳቸው መተኪያ እንዲሆኑ የተመረጡ አይደሉም። እነዚህን ንዋየ ቅድሳት ሁሉንም ለተዘጋጁበት አገልግሎት ለተመረጡበት ሥራ ስንጠቀምባቸው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የየበኩላቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። ለምሳሌ ዛሬ በመሰንቆ መዝሙርን ስናጅብ መሰንቆው የፀናፅልን ወይም የከበሮን ቦታ እንዲወስድ የተመረጠ ዕቃ ሆኖ አይደለም። ሆኖም ግን ምክንያቱ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለመሰንቆ የራሱ ድርሻ ስላለው ለዚያ ተፈልጐ ነው። እንደዚሁም ኦርጋንም/አርጋኖንም ከበሮንና ፀናፅልን እንዲያስቀር ወይም እንዲተካ የታሰበ ሳይሆን የተሰራበትን የራሱን ጥቅም እንዲሰጥ ለማድረግ ነው እንጂ።
ቤተ ክርስቲያን በብሉይ ኪዳን መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ ፭፥፲፩-፲፬ እንደተጠቀሰው በጸናጽል በመሰንቆ በበገና በዜማም ዕቃ ሁሉ የሰለጠነ የመዘምራን አካል ኖሯት እነዚህን ሁሉ አስማምታ የእግዚአብሔርን ስም እንድትቀድስበት ልዮ ልዮ የመዝሙር መሳሪያዎችን ያዘች እንጂ አንዱን በአንዱ ለማጥፋት አይደለም።

5) «የባህር ማዶ መሳሪያ ነው።»

መልሱ አይደለም ነው። አለመሆኑን ከዚህ ቀደም አይተናል። ቢሆንስ በሃይማኖት የተቀበልናቸውን ነገሮች ከአካባቢ እና ከቀለም ጋር ማዛመድ የዘመናችን ፖለቲካ ነው እንጂ ክርስቲያናዊ ነገር አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊት (እንተ ላዕለ ኵሉ) ናት። መጽሐፍ ቅዱስ በጥቁሮች ስላልተጻፈ አንቀበልም ልንል ነውን? ይህ መንፈስ ከእግዚአብሔር አይደልም።

6) ቅርሳችንን ለመጠበቅ

ቤተ ክርስቲያናችን ለሰዎች መዳን ለክርስቲያኖች እውነተኛ ሕይወት እድገት ያዋለቻቸው ነገሮች ከጊዜ በኋላ በሚያምኑትም በማያምኑትም ሕዝቦች ዘንድ የባህል መግለጫዎች መሆናቸው እውነት ነው። ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት ከሆኑ ሀብቶችዋ አንዱ አርጋኖን እንደሆነ በሚገባ ተመልክተናል። ስለዚህ በአርጋኖን መዘመር ሀብትን መጠቀም እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያን አጥፊ ነገርን ማስገባት አይደለም። አንድ አንድ ጊዜ ደግሞ ዘመናዊ መሳሪያ ስለሆነ አንጠቀምም ይላሉ። ጥንታዊነቱ አጠያያቂ ባይሆንም በዘመናዊ መሳሪያ መጠቀምም በደል አይደለም።
ቤተ ክርስቲያን ያላትን ጠብቃ እንዲሁም ምእመናን ሕይወታቸው በምስጋና የሚሞላበት፤ አእምሮአቸው በመዝሙር የሚደሰትበት፤ የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጹበት ለበጐ የሚውል ነገርን በየጊዜው እግዚአብሔር ለሰዎች ከሰጠ ትጠቀምበታለች። የኤሌትሪክን መብራት መጠቀም፤ ስልክን፣ ሬዲዮን፣ ልዩ ልዩ የኢንፎርሜሽን መሳሪያዎችን ዓለም ለፖለቲካዋ እና ለሥጋዌ እርባና ስትጠቀም ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ለበጐ ትጠቀምበታለች። ወንጌል ታስተምርበታለች። እንደዚሁ ሁሉ የመዝሙር መሳሪያም ለእግዚአብሔር ክብር ቢውል ምናልባት ሜልኮል በመቃብር ውስጥ የወለደቻቸው የመዝሙር ጠላቶች ዘማርያንን ዘፋኝ ባዮች የዳዊት ተቃዋሚዎች ካልሆኑ በቀር ምንም የሚከለክል መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያናችን የለም። ዘምሩ የሚል ግን ሞልቷል።

በመሰረቱ ሕይወት የሚድንበት ከሆነ የክርስቶስ ወንጌል የሚገለጥበት ዘፋኝ ተለውጦ ዘማሪ የሚሆንበት መሳሪያ እንደዚሁም ጥንታዊ የዜማ ዕቃ ሲሆን በኦርጋን ላይ ለምን ያላዋቂ አውጋዞች እንደተነሳሱ ግልጽ አይደለም። ቅዱስ ዳዊት ግን ባለን ነገር፣ ኃይል፣ ጥበብ ሁሉ እግዚአብሔርን እንድናመልክ ፈቅዷል። በዘመኑ የነበሩትን የመዝሙር የዘፈን ዕቃዎች ዘምሮባቸዋል። በአዲስ ቅኔ፤ ድምጽ ባለው የመዝሙር ዕቃ ሁሉ እግዚአብሔርን እንድናመልክ ተናግሯል። መዝሙር ፩፻፶ን በሙሉ ያንቡ። በዳዊት ዘመን ቢገኝ ዳዊት የእግዚአብሔር ሰው ስለሆነ ይዘምርበት ነበር እንጂ ዝፈኑበት አትዘምሩበት አይልም ነበር።

7) የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት አይደለም ይላሉ።

በአርጋኖን/ኦርጋን መዘመር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አይደለም ብሎ ቅዱስ ሲኖዶስ የወሰነበት ጊዜ እና ዘመን የለም። በአንጻሩም በአርጋኖን እንድንዘምር ቅዱስ ሲኖዶስ ያልወሰነበት ጊዜ የለም። ቤተ ክርስቲያን የዜማ ዕቃዎችዋን ስትቆጥር ከአባቶችዋ እንዳገኘችው አርጋኖንን ከተራ ቁጥር ያወጣችበት ጊዜ የለም። አርጋኖን ኦርጋን መሆኑን ማስተዋል ደግሞ የእኛ

ድርሻ ነው። ይኸውም ሊታወቅ በአዲስ አበባ ያሉ አባቶችም ሆነ በአሜሪካ ያሉ አባቶች በአርጋኖን እንዲዘመር ፈቅደዋል። በየውሳኔዎቻቸው ዝርዝር ላይ ይህንን ሳይጠቅሱ ያለፉበት ጊዜ የለም። ችግሩ የቋንቋ እንጂ የምስጢር አይደለም።

በመሰረቱ የአርጋኖን/ኦርጋን ታሪካዊ አመጣጥ ጥንታዊና በመንፈሳዊው ዓለምም ትልቅ መንፈሳዊ መሳሪያ መሆኑን ተመልክተናል። በጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም እንደሌሎች አሐት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከጥንት ጀምሮ የአርጋኖን/የኦርጋን አገልግሎት የነበረና ያለ መሆኑን ከእነ ቅዱስ ያሬድ ከእነ አባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከጥናት ጽሑፎች ከልዩ ልዩ መዝገበ ቃላት እንረዳለን። በእኛ ቤተ ክርስቲያን የአርጋኖን አገልግሎት እንደ ከበሮው እንደ መቋሚያው እንደ ጸናጽል እስከ አሁን በቅርቡ በቤተ ክርስቲያን ሲዘመርበት በሰፊው አላየንም መለት ከሆነ ጥያቄያቸው ቤተ ክርስቲያን ካሳለፈቻቸው ፈተናዎች ሊያጠፏት ተነስተውባት ከነበሩ ጠላቶችዋ (ከነጉዲት ዮዲት ከእነ ግራኝ አህመድ ከነ ድርቡሽ) ወዘተ … የተነሳ ብዙ የጥበብ የበረከት መጻሕፍቶችዋ ጠፍተዋል። አርጋኖን ብቻ ሳይሆን የመዝሙር መሳሪያዎችዋ ሁሉ ተቃጥለዋል። እንደ መሰንቆ እንደ በገና እንደ ዋሽንት እንደ እንዚራ ያሉት ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት ተሰደው ቀርተዋል።

እንዚራ እና አርጋኖን ደግሞ በመጻሕፍት ብቻ ስማቸው እየታወሰ ቤተ ክርስቲያንም የመዝሙር መሳሪያዎችዋ እንደሆኑ እያስተማረች መልካቸውንና ስማቸውን ለማዛመድ እስክንቸገር ድረስ ከቤተ ክርስቲያን እርቀው ቆይተዋል። ይህም አያስገርምም። ዛሬ እነዚህ የዜማ ዕቃዎች ብቻ ሳይሆኑ በመሰንቆ በእንዚራ በበገና መዘመርም በመጽሐፍ እንጂ በግብር በማኅሌት አገልግሎት ሲሰጥ አይታይም። ግን መጻሕፍቱ ሁሉ ይመሰክሩላቸዋል። ይልቁንም መሰንቆ ከዕቃ ቤት ወጥቶ የአዝማሪ የዘዋሪ መሳሪያ ሆኖ ሲኖር ዛሬ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ዘማሪዎች በኩል በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እየሰጠ ይታያል። ነገም ሌሎቹ እንደሱ ሊመለሱ ይገባል። በክፉ ዘመን ያጡትን ንብረት እንደ ጠፋ ይቅር ማለት ተገቢ አይደለምና። ለምሳሌ፥ እንኳንስ ይሄን ነባሩን ነገር ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ከሆነ ሁሉን ማድረግ ይገባል።

ቀድሞ ወንጌል እንደ አሁኑ ማታ ማታ ስራዬ ተብሎ አይሰበክም ነበር። አሁን ግን ያ ሆንዋል። ባሕላችን አይደለም አንልም። ቀድሞ የወጣት ሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት አልነበረም። ዛሬ ግን አለ። ባሕላችን አይደለም አንልም። ጠቃሚ ነውና። የአርጋኖን አገልግሎት ግን ከዚህ ሁሉ በተለየ መንገድ የነበረ ግን በችግር ዘመን የቀረ ነው እንጂ አዲስ ነገር አይደለም። ይኸውም ሊታወቅ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማው ዘመን በሚባለው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ከሺህ፱፻፵ዎቹ ጀምሮ እስከ ሺህ፱፻፷፰ ዓ.ም. ድረስ በቤተ ክርስቲያን ሲዘመርበት ቆይቷል። አኮርዲዮን እንዚራ ነው ብለው አበው ስለተቀበሉት በአክሱም ጽዮን በተድባበ ማርያም በቆማ ፋሲለ ደስ በደብረ ብርሃን ሥላሴ ጐንደር በማህደረ ማርያም እንደነበረ አባቶቻችን የዓይን ምስክሮች ናቸው። ይህንን ሁሉ ያተትኩት በኦርጋን መዘመር ጥንታዊ ሥርዓታችን ነው ከዚያም አልፎ ተርፎ ሁሉም ሊያውቀው የሚገባው ነገር «  » ለቅዱስ ያሬድ ዜማ በጣም ተስማሚ ለሊቃውንቱ ለዛና ጉሮሮ የዜማ ስልት የሚስማማ አብሮ የሚሄድና የሚንቆሮቆር በመሆኑ ከማንም የበለጠ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ሀብት ላላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በጣም የሚጠቅም ልዩ ሀብት ነውና ልንጠቀምበት ይገባል ለማለት ነው።

## ማጠቃለያ

እባካችሁ መደማመጥ ይኑር። አባቶችንም ምእመናንንም ግራ አናጋባ። ለሕዝቡ ሰላም እናስብ እንጂ የግል ችግራችንን የቤተ ክርስቲያን ችግር አድርገን አናቅርብ። የመደብ ትግሉ ከአውደ ምሕረት ይወገድ። የሥጋ የሥራ መስክ በቤተ ክርስቲያን ለመፍጠር ሥጋውያኑም መንፈሳዊያን ነን በሚል ፍጹም በቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ባልተገለጠ የድፍረት ሥራ በመሰማራት ለዕለታዊ ጥቅምና ክብር ስንል ቤተ ክርስቲያንን አንዋጋት። ዐይነ ልቦናችን ይብራ። ሌሊቱ አስተሳሰብ ጒህ ይቅደድበት። ጨለማ ይወገድ አለማወቅም ይራቅ። ሞቱ ሕይወት ሕይወቱም ሞት፤ ጽድቁ ኃጢአት ኃጢአቱም ጽድቅ መስሎ አይታየን። ተስማምተን ተሰብስበን በፍቅር እናምልክ እንዘምር። ክርስቶስ ለሞተለት ሕዝብም እናስብለት። በተራ ውዝግብ ቤተ ክርስቲያን የሁከት አደባባይ እንዳትመስል። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያንን አስራት ጅራፏን ከቤተ ክርስቲያን ነጥቀው ቤተ ክርስቲያንን በገንዘብዋ የሚገርፏት የጥቅም እና የንግድ ሐዋርያት አገልግሎት ያቁም።

<u>የዳዊት ልጆች ሆይ፥</u> ሜልኮልን አትምሰሚት። ዝም በሉ ብትል ወይንም ብትስቅባችሁ ሜልኮል ዓለምን እርሷት። ዝም ብላችሁ ዘምሩ። እሷም ትመክናለች። የንጉሡ የክርስቶስ አባት የሆነው የእሴይ እናት እንዳትሆንም በምክንያት ትቀጣለች። ወደ መቃብር ትወርዳለች። ከክርስቶስ ቤተሰብ ቁጥርም ውስጥ አትገባም። ግብዝነቷ ያጠፋታል።
ጥቅም ያሳወራት ያሰከራት የአንድ አንድ ክርስቲያን መሰል ቢጽ ሐሳውያን ወጣቶች ልብ ሜልኮልን ደስ ባይላትም ቤተ ክርስቲያን በሚቻላት መንገድ ሁሉ ፈጣሪዋን ታመልካለች፤ ለምስጋና ተፈጥራለችና።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር …. አሜን

*በመምህር ልዑለ ቃል አካሉ*